# በሰሜን ሸዋ ዞን፣ ልማዳዊ  የባና እና የበርኖስ አሰራር ቅረሳና ገለፃ

**መንግስቱ ታደሰ**[1]

**አህጽሮተ ጥናት**

ይህ ጥናት በሰሜን  ሸዋ ዞን፣ በመንዝ ጌራ እና በመንዝ ማማ ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች ላይ ያለውን ልማዳዊ የባና እና የበርኖስ አሰራር፣ ተግባር እና ማህበራዊ ፋይዳ በመቅረስ እና በመግለጽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የምርምሩን አላማ ለማሳካት የመስክ ምልከታ፣ ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ጥናቱ በስራው ላይ ልምድ ያካበቱ እና በእድሜ የገፉ የመረጃ አቀባይ ባለሙያዎችን በመቅረፀ-ትእይንት እና በመቅረጸ-ድምጽ ታግዞ መረጃዎችን በመውሰድ እና ከዚህ በፊት በድምጽ ወምስል የተቀረጹ ስራዎችን እንደ ቅደም ተከተላቸው የቀዳማይ እና የካልዓይ የመረጃ ምንጮችን አገልግሎት ላይ አውሏል፡፡ የባና ባለሙያዎቹን ለመምረጥ አላማ-መር (purposive)፣ እንዲሁም ስለቀድሞ የባና ምርት ልምድና ንግድ ሥራ ታሪክ አዋቂ ሰዎችን ለመምረጥ ደግሞ ተሰናሳይ ጥቁምታ (Chain referral) የንሞና ዘዴዎችን ጥናቱ ተጠቅሟል፡፡ ሶስት ማዕዘናዊነት ዘዴን በመጠቀም በሁሉም ሂደቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛነት ተመዝኖ እና ተጣርቶ ትንተናው በገለፃ መልክ ተከናውኗል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው አገር በቀል እውቀቱ ለዘመናት ምንም አይነት መሻሻል ሳይደረግበት እየተሰራበት በመሆኑ የመጥፋት አደጋ ከተጋረጠባቸው ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች ሊያሳመድበው ችሏል፡፡ የስራው ሂደትም ጥንታዊ፣ አድካሚ፣ አሰልቺ እና በቂ ገቢ የማያስገኝ በመሆኑ ጥበቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ መጥቷል፡፡ በተጨማሪም አብዛኞቹ ነባር ባለሙያዎች የሚሰሩበትን እቃ ሰቅለው የግብርና ስራውን ያከናወኑ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ ከባና እና ከበርኖስ ሙያ ይልቅ ነባሩን እቃ በማስተካከል የሸመናውን  ሙያ በቀላሉ ለምደው እየሰሩ እንደሆነና ከበፊቱ የበለጠ የገቢ ምንጭም እንደሚያገኙበት የመስክ ማስረጃዎቹ ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም የባና እና የበርኖስ ሙያ ረዘም ያለ ታሪክ ያለው፣ ከሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች በተለየ መልኩ የጥበብ፣ የእምነት እና የማንነት መገለጫ እንደመሆኑ መጠን የአሰራር ሂደቱንም ሆነ የምርቱን ጥራት ከሌሎች ሀገሮች ልምዶችን በመውሰድ የማዘመን ስራ በመስራት እንዲሁም ህልውናውን አጠናክሮ በማስቀጠል ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ አስፈላጊ ነው፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** ባና፣ በርኖስ፣ ልማዳዊ አሰራር

## 1. መግቢያ

በአለም ላይ ካሉት ቋንቋዎችና ልማዳዊ አገር በቀል እውቀቶች መካከል በርካቶቹ የመጥፋት እና የመቀየር አደጋ የተደቀነባቸው ሲሆን አንዳንዶቹ

[1] ረዳት ፕሮፌሰር፣ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ: mtadesse66@yahoo.com

ደግሞ በሞት አፋፍ ላይ እንደሆኑ በርካታ ጽሁፎች ያስረዳሉ (Hale, 1998; UNESCO, 2003)። እነዚህ ቋንቋዎችና ባህላዊ ገፅታዎች በሚጠፉበት ጊዜም በውስጣቸው ያቀፉትን ታሪካዊ ቅርስ፣ ፍልስፍና፣ ማንነት፣ ጥበባዊ ፋይዳ፣ ስነቃል፣ ወዘተ. ይዘው ይሞታሉ፡፡ በሀገር በቀል እውቀቶች ላይ የሚደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሉላዊነት፣ በቴክኖሎጂ ማደግ እና በፈጣን የከተሞች መስፋፋት ሂደት ሳቢያ ባደገውም ሆነ በማደግ ላይ ባለው አለም በርካታ ገፅታዎቻቸው በመቀየር እና በመጥፋት ላይ እንደሆኑ Adedamola (2017) ያስረዳል። ስለዚህ የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸውን ቁሳዊ ሀገር በቀል እውቀቶችን መመዝገብና መሰነድ ለተተኪው ትውልድ በቀላሉ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ሚና ይጫወታል (WIPO Publication No. 913 (E), p.)።

ኢትዮጵያም የበርካታ ቋንቋዎች እና የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶች ባለቤት ብትሆንም አብዛኞቹ በመጥፋት አደጋ ላይ እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እንዲህ አይነት ችግር ከተጋረጠባቸው ሀገር በቀል እውቀቶች መካከል በሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙት የመንዝ ወረዳዎች ውስጥ የሚተገበረው፣ ሊጠፋ የተቃረበው እና በልማዳዊ መንገድ የሚከናወነው የባና እና የበርኖስ ምርት አንዱ ሲሆን በተመራማሪዎች ዘንድም ትኩረት ሳይሰጠው ለረዥም ዘመናት ቆይቷል፡፡ ባህላዊ አልባሳቱን የሚሰሩትም ሆነ የሚጠቀሙበት ሰዎች የእደ-ጥበብ ስራውን እንደ ልዩ መታወቂያቸው እና ተምሳሌታዊ መገለጫቸው አድርገው የመውሰድ የረጅም ጊዜ ልምድ አላቸው፡፡ ይህን የተደራጀ ልምድ እንደ እድል በመጠቀም፣ ሙያውን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍና ህልውናውንም አጠናክሮ ለማስቀጠል በጥናትና ምርምር በመመስረት እና በፕሮጀክት በመደገፍ መፍትሄ ማፈላለግ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ቁሳዊ ሀብቱ ከማህበራዊ፣ ከመንፈሳዊና ከባህላዊ ፋይዳዎች በተጨማሪ የፈጠራ ኪን ምንጭ በመሆን ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን በመረዳት ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ሊከናወን በቅቷል።

## 1. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙት መንዝ ጌራ እና መንዝ ማማ ወረዳዎች ውስጥ የሚከናወነውን የባና እና የበርኖስ ልማዳዊ ስራ በመቅረስ እና ሂደቶችንም በመግለፅ ላይ ያተኮረ ሲሆን የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች አሉት።

- የዕደ-ጥበብ ምርቱን በተመለከተ የሚነገሩ ታሪኮችን፣ አፋዊ ትረካዎችንና ሥነቃሎችን መቅረስና መግለጽ፣
- በምርቱ ሂደት ውስጥ ስራ ላይ የሚውሉ መሳሪያዎችን መቅረስ እና አገልግሎታቸውን መለየት፣
- የምርቱን የተለያዩ የሂደት ደረጃዎች መለየት እና መግለጽ ፣
- ምርቶቹ የሚሰጡትን አገልግሎት መለየት፣
- በማምረት ተግባሩ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን መለየት እና

- የምርቱን ታሪካዊ ዳራ እና ከሌሎች አካባቢዎች ጋር ያለውን ግንኙነት መፈተሽ ናቸው፡፡

## 2. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የአገር በቀል እውቀትን ትርጓሜ እና ፋይዳ የሚገልጽ በመሆኑ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚከተል ነው፡፡ እንዲህ አይነቱን ልማዳዊ የአሰራር ሂደት ባግባቡ ሰንዶ እና ገልጾ ማስቀመጥ የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ህይወት ለመቀየር፤ ትውልዱን ለማስተምር፣ ንቁና ጥበበኛ ለማድረግ፣ ውስጣዊ ስሜቱን ለመግለጽ እና ባህሉንም ጠብቆ ለማቆየት ሁነኛ ሚና ይጫወታል (Sims & Stephens, 2005)፡፡ የምርምር ስራው የሚከተለው ሞዴል ባህልን፣ ማህበራዊ መዋቅርን እና ማህበራዊ አገልግሎትን ለመረዳት የሚያገለግለውን የፋይዳዊነት ንድፈሃሳብ (functionalism theory) ነው፡፡ በዚህ ንድፈ-ሀሳብ እይታ አንድ ባህል ባህል ሆኖ ለመቀጠል ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አንዳች አገልግሎት ይኖራል የሚል እምነት ከመኖሩም ባሻገር የተለያዩ ማህበራዊ ክስተቶችን ይዳስሳል፡፡ ይህ ንድፈ-ሀሳብ የሚታዩ ቁሶችን ለመተንተን ከሚያግዙ ሞዴሎች መካከል አንዱ ሲሆን በባህላዊ መንገድ የሚሰሩት እቃዎች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ፣ የሚሰጡት አገልግሎት ምን እንደሆነ እና በስራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ የሚኖራቸውን ተደራራቢ ትርጉም በመግለጽ ላይ ትኩረት ያደርጋል (Prown, 1982)፡፡

እንደ Ihatsu (2002) ገለጻ የዕጅ ስራ ልማዳዊ ጥበቦችን በሁለት አይነት እይታ መመልከት እንደሚቻል ያስረዳል፤ ይኸውም የስራ ሂደታቸው ባህሪ ምን እንደሚመስል እና ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ያላቸው ሀሳብ፣ አመለካከት እንዲሁም አላማ የሚሉ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው ጉዳዮች ከፎክሎር ዘርፎች መካከል አንዱ በሆነው ቁሳዊ አገር በቀል እውቀት ውስጥ የሚጠቃለሉ እና የጥናቱን መሰረታዊ ዓላማዎች ለማሳካት መሰረት የሚጥሉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በአካባቢው የሚመረተው ልማዳዊ የባና እና የበርኖስ አሰራር ያለውን ማህበራዊ እና መንፈሳዊ ፋይዳ እንዲሁም የአሰራር ሂደት በመግለጽና በመሰነድ ላይ ነው፡፡

## 3. የመረጃ መሰብሰቢያ እና የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች

የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡ ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ ምልከታ፣ቃለመጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት አገልግሎት ላይ ውለዋል (Goldstein, 1964፣ 77-104፤ ፈቃደ፣ 1991፣90)፡፡ ከዚህም ሌላ ምርምሩ ከአካባቢው ማህበረሰብ በመቅረፀ-ትእይንት (በምስል ወድምጽ)፣ በመቅረጸ-ድምጽ የተቀዱ እና ከዚህ በፊት ተቀርሰው የተቀመጡ (ከመቅረፀ-ትእይንት የተወሰዱ ምስሎች) ሰነዶችን ተጠቅሟል፡፡

ምልከታን በመጠቀም የባና እና የበርኖስ ሥራ ባለሙያዎች የአመራረት ሂደት ከተፈጥሯዊ መቸታቸው ጋር መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን በድምጽ ወምስል ቀረፃ የታገዘ ያልተገደበ (open-ended) ነጻ እና ተሳትፏዊ ምልከታም ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በስርዓታዊ ምልከታው የተገኙት የዕደ-ጥበብ ሙያው አሰራርና ተያያዥ ጉዳዮች የተሟላ እና ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲሰነዱ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ ልማዳዊ የባና ሥራ በማን፣ መቼ እና እንዴት እንደሚዘጋጅ እንዲሁም ማህበራዊ ትርጓሜው እና ፋይዳው ምን እንደሚመስል ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በመከታተል በመቅረፀ-ትእይንት፣ በመቅረጸ-ድምጽ እና በማስታወሻ ላይ ተቀርሰዋል፡፡

ቃለመጠይቅ በምልከታ ወቅት ለተሰበሰቡት መረጃዎች ድጋፍ ለመስጠት፣ ቀደምት ሁነቶችን እና ታሪኮችን አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ ታስቦ  የተዘጋጀ ነው፡፡ ቃለመጠይቁ በሁለት መንገድ የሚካሄድ ነው፡፡ ከምልከታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማጠናከር የተደራጀ ቃለመጠይቅ (semi-structure interview)፣ ታሪካዊ ሁነቶችን በተመለከተ ደግሞ ያልተዋቀረ ጥልቅ ቃለ መጠይቅ (unstructured in-depth interview) አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ በቃለመጠይቁ የተሳተፉ ሰዎችን በአላማ ተኮር እና በጠቁምታ ምሪት (Chain referral) የናሙና አወሳሰድ ዘዴ 33 ሰዎች እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የጥናቱ አካላት በሙያው ለረዥም ጊዜ የቆዩ፣ ታሪክ አዋቂ እና የእድሜ ባለጸጋ የሆኑ፣ ከጥናቱ ጋር አግባብነት ያላቸው የባህልና ቅርስ ባለሙያ የሆኑ ናቸው፡፡

ተተኳሪ የቡድን ውይይት በአብዛኛው የምንጠቀመው በምልከታም ሆነ በቃለ መጠይቅ ያልደረስንባቸው እና የተለየ መረጃ እንደምናገኝ እርግጠኛ ስንሆን ነው፡፡ Kruegor (1994) ተተኳሪ የቡድን ውይይት አባላት ከ8-12 ቢሆን የተሻለ መረጃ መሰብሰብ ይቻላል በሚለው ሐሳብ መሰረት ስምንት ሰዎችን የያዘ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ተከናውኗል፡፡ በቡድን ውይይቱ የተሳተፉት ሰዎች ስለሚጠየቁት ጥያቄ ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው፤ ታሪኩን እና ባህሉን የሚያውቁ ወዘተ. ባለሙያዎችን በመምረጥ ስራው ተካሂዷል፡፡

በሰሜን ሸዋ ውስጥ የሚገኙት መንዝ ማማ፣ መንዝ ጌራ፣ መንዝ ላሎ፣ እና መንዝ ቀያ ወረዳዎች ካላቸው ደጋማ የአየር ንብረት የተነሳ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በተለየ መልኩ የባና፣ የበርኖስ እና የስጋጫ ምርቶች ይከናወኑባቸው እንደነበር በወፍ በረር ጥናቱ ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነገርግን መንዝ ላሎ እና መንዝ ቀያ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች በእድሜ መግፋት ምክንያት ያቆሙ፣ በገበያ እጥረት ምክንያት ስራውን የማይሰሩ እና ሙያውንም ባግባቡ ለትውልድ ለማስተላለፍ ጥረት ያላደረጉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በእነዚህ ቦታዎች ያለው የስራ እንቅስቃሴ በጣም የቀዘቀዘ ስለሆነ ከምርምሩ ውጭ ሆነዋል፡፡ ስለዚህ ጥናቱ በመንዝ ማማ እና በመንዝ ጌራ ወረዳዎች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

የምርምሩን ባህሪ መሰረት በማድረግ ጥናቱ የተጠቀመባቸው የንሞና ዘዴዎች ሁለት ሲሆኑ አላማ መር (purposive) እና ተሰናሳይ ጥቆማ (chain referral) ናቸው፡፡ በአላማ መር ንሞና የባና ባለሙያዎችን፣ በተሰናሳይ ጥቆማ ደግሞ ስለቀድሞ የባና ምርት የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው እና ታሪክ አዋቂዎች ተመርጠዋል፡፡

## 4. የጥናቱ ትንተና

ቁሳዊ ባህልን መሰረት ያደረገ ጥናት በሶስት መንገድ ሊተነተን እንደሚችል ፕሮውን ይገልፃል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ቁሳዊ ባህል በመሆኑ Prown (1982) ካሰፈራቸው ገለፃ (Description)፣ ትርጓሜ (Deduction) እና ጥቆማ (speculation) መካከል የጥናቱን አላማ እና የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ገለፃ (Description)ን ለትንተናው ተጠቅሟል፡፡

### ለበርኖስ እና ለባና ስራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች

**ደጋን እና ጅማት**:- ደጋን ከተለያየ እንጨት ተቆልምሞ የሚሰራ ነው፡፡ ደጋኑን ወጥሮ የሚይዝ፣ ንዝረትን የሚፈጥር እና የበጉን ጸጉር የሚያባዝተው ደግሞ ጅማት ይባላል፡፡ ጅማት የሚሰራው ከበግ አንጀት ሲሆን፣ አንጀቱ ታልቦ በጥፍር እና በእንጨት እንዲቀጥን ከተደረገ በኋላ ይላጋል፤ ተወጥሮ ይገመዳል፤ ለሁለት ታጥፎ ይከረራል ወይም ይጦዛል፣ ተወጥሮ ከታሰረ በኋላ ቀጭን መሆኑ ሲረጋገጥ በቀላሉ እንዳይቆረጥ በላት ወይም በሞራ በመቀባት እንዲርስ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም ጅማቱ በደጋኑ (በቆላፋው እንጨት) ላይ ተወጥሮ ይታሰራል፡፡



ምስል 1፡- ደጋን እና ጅማት

**መታረሪያ**:- ጠንካራ እና ቀጭን ሆና ከወይራ፣ ከቀጨሞ፣ ከጎሽ መቃ፣ ከፍየሌ-ፈጅ እና ቀለል ካሉ እጽዋት እንደምትሰራ አባቶች ያስረዳሉ፡፡ መታረሪያ በስራው ሂደት የእናቶችን አውራጣት ወጥራ እንድትይዝ እና ጅማቱን ከደጋኑ ጋር በማያያዝ በቅል አንገቱ (ምስል ሁለትን ይመልከቱ) አማካኝነት ንዝረቱ እንዲፈጠር እና እንዲከር በማድረግ የሚነደፈውን ጸጉር ባግባቡ እንዲባዝትና እንዲለሰልስ የምታደርግ መሳሪያ ናት፡፡



ምስል 2፡- መታረሪያ

**ቅል አንገት:-** ከፍተኛ ንዝረትን በመፍጠር እና ንዝረቱ እንዲከር በማድረግ `ድር …ድር…ድር…` የሚል ድምጽ በመፍጠር ቆርበቱ ላይ የተቀመጠውን ጸጉር እንዲልም የምታደርገው መሳሪያ ቅል አንገት ትባላለች፡፡ ይህች መሳሪያ ቆላ አካባቢ ከሚበቅል የቅል ተክል የምትሰራ ሲሆን ከላይ ተቀርፍፋ ሲትቆረጥ ቅል አንገት፣ ከታች የምትቀረው ክፍል ደግሞ ለጠላ መጠጫ ግልጋሎት የምትውል ሽክና ወይም አንኮላ ትሆናለች፡፡



ምስል 3፡- ቅል አንገት

**የጸጉር እንዝርት፡-** ከጥጥ እንዝርት ከፍ ያለች እና እንጨቱ ቅርቀሀ ከተባለ ተክል፣ ክቧ ነገር ደግሞ ከጎሽ ቀንድ ይሰራሉ፡፡



ምስል 4፡- የጸጉር እንዝርት

**አንከርት፡-** የተኮበውን ድር በትናንሽ ቀሰሞች የሚጠነጠንበት ከእንጨት የተሰራ መሳሪያ ነው፡፡ ከዚህ በታች ባለው ምስል እንደሚታየው በዚህ መሳሪያ ድሩ ይደወራል፡፡



ምስል 5 ፡- አንከርት

**ጥርስ (ሰፈፍ) እና መን፡-** ጥርስ ድሩ እና መኑ ተዋዶ በእያንዳንዱ ክፍተት ተቆጥሮ እንዲገባ በማድረግ ስራውን ለመጀመር ምቹ መደላድል የሚፈጥር መሳሪያ ነው (የ "ሀ"ን ምስል ይመልከቱ)፡፡ ከዚህ በታች በፎቶ (ምስል "ለ") የሚታየው መን ስራው ሲጀመር ቁጢቱ ወይም ድሩ ወይም ክሩ ይቋጠርበታል፤ ሲያልቅ ደግሞ ቋጠሮው ይፈታል፡፡

ሀ.  ለ. 

ምስል 6፡- ጥርስ እና መን

**መምቻ፡-** ባለሙያው ድሩን በመወርወሪያ እየመላለሰ ከወዲያ ወዲህ እያለ ሲያስገባ ባናው ወይም በርኖሱ ይጠብቅ ዘንድ የሚመታበት መሳሪያ ሲሆን ከጥርሱ ወይም ከሰፈፉ በላይ ይገኛል፡፡ ከመምቻው በታች ጥርሱ ከጀርባው ደግሞ መኑ እንደሚገኝ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡



ምስል 7፡- መምቻ

**ቀሰም እና መወርወሪያ፡-** ቀሰም ከቅርከሃ የሚሰራ ሲሆን የባናው ወይም የበርኖሱ ድር ወይም ክር የሚጠነጠንበት መሳሪያ ነው፡፡ ቀሰሟ ድሩ ከተጠነጠነባት በኋላ ከታች በምስሉ እንደሚታየው መወረወሪያው ውስጥ በሽቦ መሰል ነገር ትገባለች፡፡ መወርወሪያዋ የምትሰራው ከእንጨት ነው፡፡ መወርወሪያዋ በጎኗ ላይ ባለችው ቀዳዳ ድሩ ይወጣና ከመኑ ጋር ትቋጠራለች፤ ከዚያም ባለሙያው ስራውን ይጀምራል፡፡




ምስል 8፡- ቀሰም እና መወርወሪያ

**መቂናጥ (ማመላለሻ) እና መርገጫ፡-** የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ መቂናጦች እና ከእነሱ ቀጥሎ ያለው የእግር መርገጫ ለባናው ወይም ለበርኖሱ ልብስ ሆኖ መውጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ በግራ በኩል ያለው መርገጫ ሲረገጥ በግራ በኩል ላለው መቂናጥ ሰላምታ ሲያቀርብ፣ በቀኝ በኩል ያለችው መቂናጥ ደግሞ በተራዋ ለመርገጫው በመስገድ ምላሽ እንደምትሰጥ ባለሙያ አባቶች አስረድተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ቀሰሙን በውስጧ የያዘችው መወርወሪያ ያለረፍት ከወዲያ ወዲህ ትሯሯጣለች፡፡



ምስል 9፡- *መቂናጥ እና መርገጫ*

***መጠቅለያ እና ቁጭምብር፡-*** *መጠቅለያው ከእንጨት የሚሰራ ሲሆን እንዳይፈራ (እንዳይሰነጠቅ) በቆዳ ይለጎማል፡፡ ባለሙያው የተወሰነ የባና ወይም የበርኖስ ልብሶች በሚሰራበት ሂደት እየረዘመ በሚመጣበት ጊዜ የሚጠቀለልበት መሳሪያ ነው፡፡ መጠቅለያ በቀኝ በኩል አራት ቀዳዳዎች ያሉት ሲሆን ከዚህ በታች ቆም ብላ በምትታየው ቁጭምብር በምትባለዋ መሳሪያ የሚሰራውን ልብስ እየጠቀለለ እና እያስገባ ስራውን ያከናውናል፡፡*





ምስል 10፡- *መጠቅለያ እና ቁጭምብር*

**የበርኖስ እና የባና በጎች ምርጫ**

*የመንዝ በጎች የሚታወቁት በጸጉራቸው ብዛት ነው፡፡ የአካባቢው ህብረተሰብ ይህን እንደ እድል በመውሰድ የተለያዩ የባና እና የበርኖስ አልባሳትን በማምረት ከቀዝቃዛው የአየር ንብረት ጋር ተስማምቶ ሲኖር ቆይቷል፡፡ ጸጉራቸው ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉ በጎች ደግሞ አንድ አይነት አይደሉም፤ እንደ በጎች እድሜ እና የጸጉር ቀለም (ጥቁር፣ ነጭ፣ ዳልቻ፣ ቀይ) ይለያያሉ፡፡*

*ከታች በፎቶ `ሀ` እና `ለ` ላይ እንደሚታየው ለበርኖስ ስራ የሚውለው የበግ አይነት በጣም ጥቁር፣ ቄብ ወይም ባካባቢው አጠራር `ሪዝ` ወይም ጠቦት በግ ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚላጨው ጸጉር ነው፡፡ የእነዚህ የበጎች እድሜ ከስድስት እና*

ከሰባት ወር የማይበልጥ በመሆኑ ጸጉራቸው በጣም የለሰለሰ ነው፡፡ ለባና እና ለስጋጫ የሚያገለግለው የበግ ጸጉር ግን እንደሚፈለገው የምርት አይነት (ነጠላ፣ ብርድልብስ፣ ያልጋልብስ፣ መጋረጃ፣ ስጋጫ ወዘተ.) ከትናንሽ እስከ ትላልቅ በጎች ድረስ በተደጋጋሚ እየተቆረጠ ስራ ላይ ይውላል፡፡ በፎቶ `ሐ` ላይ ያሉት በጎች ሁሉ ለዚህ ተግባር የምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡ ለበርኖስ ተብለው የሚዘጋጁ ጥቁር በጎች በጥንቃቄ የሚመረጡ ከመሆናቸውም ባሻገር እንደልብ በየቦታው የምናገኛቸው አይደሉም፡፡

ሀ.  ለ.  ሐ. 

ምስል 11፡- ጸጉራቸው ለበርኖስና ለባና መስሪያ የሚሆኑ በጎች

**የበርኖስ እና የባና ምርቶች አሰራር ሂደት**

ከበጎች ምርጫ እና ከሚደረግለት ጥንቃቄ በስተቀር የበርኖስ እና የባና ምርቶች አሰራር ሂደት ተመሳሳይ እንደሆነ በሙያው ውስጥ ያሉ አባቶች ያስረዳሉ፡፡ ለበርኖስ የሚሆኑ በጎች ከተመረጡ በኋላ ባካባቢው ባለ ንጽህ የወንዝ ውሃ ከታች በፎቶው እንደሚታየው በጥንቃቄ ይታጠባሉ፡፡ የአጠባው ስርዓት ከዚህ በፊት ለባና መስሪያ የሚያገለግሉ በጎች በታጠቡበት ቦታ አይደረግም፡፡ ምክንያቱም በክንዋኔው ሂደት ከዚህ በፊት የታጠቡ የተለያየ ቀለም ያላቸው ጸጉሮች ቅሪት ካሁኖቹ ጋር ይቀላቀላል የሚል እምነት በመኖሩ ነው፡፡



ምስል 12[2]፡- በጎች በተዘጋጀላቸው ቦታ ሲታጠቡ

[2] EBS TV, 2019.

በጎቹ ታጥበው ከደረቁ በኋላ ቆሻሻ እንዳይነካቸው ንጹህ ቦታ ተፈልጎ ወይም ባካባቢው አጠራር ድብዳብ ላይ በማስተኛት ቀልመም ባለ ቢላዋ መሰል ነገር በ `ሀ` እና በ `ለ` ፎቶ ላይ እንደሚታየው የጸጉር ቆረጣው ይከናወናል፡፡ የተቆረጠውን ጸጉር ደግሞ ማዳበሪያ ወይም ቆርበት[3] ላይ ያስቀምጡታል (ፎቶ `ሐ`ን ይመልከቱ)፡፡




ምስል 13[4]፡- የበጎች ጸጉር ታጥቦ ከደረቀ በኃላ ሲሸለት ወይም ሲቆረጥ

ከዚህ በላይ የነበረው የስራ ሂደት የተከናወነው በወንዶች ነው፡፡ በመቀጠል የተቆረጠው ጸጉር ተራግፎ፣ ተጸድቶ እና ባግባቡ ተሰብስቦ እንዲሁም በንጹህ እቃ ላይ ተቀምጦ ለሴቶች ይሰጣል፡፡ ቀጥሎም በ `ሀ` ላይ እንደሚታየው ሲቆረጥ የተያያዘው ጸጉር ይፈለቀቃል ወይም ይፍታታል፤ ከዚያም በ`ለ` እንደተመለከተው ደጋን (ፎቶ`ሐ`ን ይመልከቱ) በሚባለው መሳሪያ (ምስል `ለ` ላይ እንደተመለከተው) ቆርበቱ ላይ ጸጉሩን በማስቀመጥ ይነደፋል፡፡




ምስል 14፡- የበጎች ጸጉር በዕጅ ሲፍታታ እና በደጋን ሲነደፍ

[3] ከከብት ቆዳ የተሰራ ምንጣፍ
[4] EBS TV, 2019.

ቀጥሎም ጸጉሩ የሚቀመጠበት ቆርበት አበጥ እንዲል ወይም ኮረብታ እንዲፈጥር ድብዳብ ወይም ትራስ ከስር ይደረግና ጉብታው ላይ ጸጉሩን በማድረግ ለተወሰነ ደቂቃ ይዳመጣል፡፡ ከዚያም የደረቀው የበግ ጸጉር በመንደፊያ መሳሪያዎች (ደጋን፣ ጅማት፣ ቅል አንገት፣ መታረሪያ) በመጠቀም ቆርበቱ ላይ የተቀመጠው ጸጉር ድርርር…ድርርር.. የሚል ድምጽ በመፍጠር እያባዘቱ እንዲልም ከተደረገ በኃላ አመልማሎ (ጸጉሩን አሽሞልሙሉ ማድቦልቦል) ይሠራል፡፡ በዚህን ጊዜም ሴቶቹ ድርርር…ድርርር.. በሚለው ድምጽ እየታጀቡ፡-

ተው እርጋ እርጋ አንተ የመንዝ ጸጉር፣
ተው እርገጥ እርገጥ እርገጥ፣
አትንቀጥቀጥ ትወጣለህ ደጋ፣
ባለህበት እርጋ እርጋ እርጋ….ይላሉ፡፡[5]

እየተንሸራተትክ አትውረድ፤ እዚያው ላይ ረግጠህና ረግተህ ላም ለማለት ታስቦ የተገጠመ ግጥም ነው፡፡ ሌሎች ሴቶች ደግሞ፡-

ሸማኔ ሸማኔ ሸማኔ ልስልሱ፣
እንደመወርወሪያው ያመላልሰኝ እሱ፡፡
ሸማኔ ቢሰራኝ ዶሎኛል ለመኑ፣
ለሰለሰኝ ብሎ ቢተወኝ ለምኑ፡፡
ለሰለሰኝ ብዬ መች እተውሻለሁ፣
በጥሽ ቀጥዬ ማግ አረግሻለሁ፡፡[6]

ከዚህም ሌላ፡-

እኔ ልጅ አንተ ልጅ ሁለታችን ለጋ፣
እምድር (ከምድር) እነኛ (እንተኛ) እይ (እንጂ) አይችለንም አልጋ፡፡
አፋፍ ላፋፍ ስሄድ አገኘሁ መቀስ፣
እኔ ልጅ ነኝና እማልጠቀስ፡፡
አንተ አልጋው ላይ ተኛ እኔ መደቡ ስር
እደርስብሃለሁ ከፍ ስል ከፍ ስል…[7] እያሉ በመዝፈን ስራቸውን በተነሳሽነት እንደሚያከናውኑ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ከዚህ በኃላም እናቶች የተባዘተውን ጸጉር በደንብ መላሙን ካረጋገጡ በኂላ እንዝርት (የጸጉር እንዝርት) በምትባለዋ መሳሪያ አመልማሎውን ይዘው ይፈትሉታል፤ በዚህ ጊዜ ወደ ቀኝ ተፈትሎ የነበረው የበግ ጸጉር በተቃራኒዉ ወደ ግራ ይከረራል፤ ልቃቂትም ይወጣዋል (ከ`ሀ` እስከ `ሰ`ን ያለውን ምስል ይመልከቱ)፡፡ በማስከተል

[5] አስማረች መንገሻ (ፈ.ታ.ይ)
[6] ሙሉእመቤት ገስጤ (ፈ.ታ.ይ)
[7] ሙሉእመቤት ገስጤ (ፈ.ታ.ይ)

የተፈተሉትንና የተመረጡትን የሁለት ልቃቂት ጫፍ አንድ ላይ በመያዝ እና በማጠንጠን ይኮባል፤ መወፈሩን እና ለእጃቸው መመጠኑን ሲመለከቱ ደግሞ ይቆርጡታል፡፡ ከዚያም የሁለቱን ልቃቂት ክሮች አንድ ላይ ወደኋላ በማክረር በእንዝርቷ ያጠነጥኑታል (`ሐ`ን ይመልከቱ)፣ ብዛቱ መጠኑ ላይ ሲደርስ ልቃቂት ሆኖ ይደራል (የ`መ` ምስል ይህን ያሳያል)፡፡ በመጨረሻም የተከረረው ለብቻው በኩብ መልክ ይጠነጠናል፡፡



ሀ. ለ ሐ. መ. ሰ.

ምስል 15[8]፡-የተፍታታው የበጎች ጸጉር በእንዝርት ሲፈተል እና ልቃቂት ሲሆን

ከዚህ በታች የተቀመጡት ቁሶች ባናንም ሆነ በርኖስን ለመስራት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በ `ሀ` እና በ`ለ` ላይ የምናያቸው የተጠነጠኑ ኩቦች ናቸው፡፡ በውስጣቸውም ዳልቻ፣ ነጭ እና ለበርኖስ የሚያገለግሉ ጥቁር ኩቦችን ይዘዋል፡፡



ሀ. ለ.

ምስል 16፡- የተከረረው ልቃቂት ወደ ኩብነት ሲቀየር

[8] ምስል 13፣ “ሀ፣ለ፣መ እና ሰ” ከ EBS TV, 2019 የተወሰዱ ናቸው፡፡


በምስል 15 “ሀ” ላይ እንደሚታየው የተኮበው ድር ከእናቶች ወደ ባለሙያዎች ዘንድ ይሄድና ዛፍ ላይ ተደርጎ ይደራል፡፡ ከዚያም ከዚህ በታች በ “ለ፣ሐ እና መ” ምስሎች ላይ እንደሚታየው ደግሞ የተኮበውን ድር ውል በመፈለግ እና አንክርት በተባለው መሳሪያ አማካኝነት በትናንሽ ቀሰሞች ይጠነጠናል፤ የማጠንጠኑ ሂደትም ማዳወር ሲባል (“ሐ” እና “መ” ይህን ሂደት ያሳያሉ) የተጠነጠነው ነገርም ድውር ወይም ማግ ይባላል፡፡




ሀ. ለ. ሐ. መ.

ምስል 17፡- ልቃቂቱ ዛፎች ላይ ታስሮ ከተደራ በኃላ በትናንሽ ቀሰሞች ሲጠነጠን

ከዚያም ድሩ ተቆጥሮ በመኑ ውስጥ ይገባል፤ ሁለት ሁለቱ አምሳ ጥንድ ከሆኑ በኂላ አንዱ ሰው በመኑ ሌላው ደግሞ በጥርሱ በኩል ሆነው በሽቦ መሰል ነገር ወደ ውስጥ እንደ ባል እና ሚስት ተዋደው እንዲገቡ ከተደረገ በኂላ (ስማቸውም ባል እና ሚስት ነው) ሁሉም ነገር ዝግጁ ሲሆን ስራው ይጀመራል፡፡ ከዚህ በፊት ግን ድሯ እየተበጠሰች በመታሰር ከመምቻው ጋር ትያያዛለች፡፡ ከዚያም በጥርሱ በኩል ቀጭን እንጨት በመኑ ጥርስ ውስጥ በመክተት ድሩን ስባ ስታመጣለት ባለሙያው እየጎተተ እየጎተተ (ይህ ሂደት ቀበሎ ይባላል) በማስገባት ሁሉንም ሲጨርስ በባህላዊው አባባል ተቆጠረ ይባላል፡፡ ክንዋኔው በተካሄደበት እለት እናቶች እና አባቶች በልማዳቸው መሰረት ሂደቱን ላከናወኑት ባለሙያዎች ከሚሰሩት ስራ ክፍያ በተጨማሪ የቆጣሪ ተብሎ አይነ ቡርቲ ወይም ድፎ ዳቦ አንዳንዴም አረቂ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ሂደት ከተከናወነ በኂላ በቀሰም የተጠነጠነውን ድር መወርወሪያ ውስጥ በማስገባትና ክሯን በቀዳዳዋ ውስጥ በማውጣት እና ከመኑ ጋር በመቋጠር ስራው ይጀመራል (ከዚህ በታች ያሉት ፎቶዎች ለዚህ ማሳያ ናቸው)፡፡




ምስል 18፡- ድሩ ተቋጥሮ በሽቦ መሰል ነገር በመኑ ውስጥ ሲገባ እና ሲቆጠር




ምስል 19፡- ቀሰሟን በመወርወሪያው ውስጥ በማስገባት ለስራ ዝግጁ ሲሆን




ምስል 20፡- ባለሙያው በስራ ላይ (ሙሉ ገጽታው)

ከላይ ባለው መልኩ ባለሙያው ሰርቶ ከጨረሰ በኋላ ይቆርጠዋል፣ ወይም ከመኑ ላይ ይለያየዋል፡፡ በዚህን ጊዜም፡-

አቡጊዳ ለባሽ ናና ባላባቱ፣
ይኸ ካኪ ለባሽ ሌባ ነው በጭራሽ፡፡
የደገኛ ልጅ ነኝ የባለባናው፣
ሳትጋግረው ሄደች ልቤን አቡክታው፡፡[9]…እያሉ ያንጎራጉራሉ፤ እንዲህ አይነቱን ስነቃላዊ ግጥም በሚያዜሙበት ጊዜም ስራውን ለማከናወን በቂ ኃይል እንደሚያገኙ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በታች በፎቶ የተመለከቱት አልባሳት ከመስሪያ እቃው አልቆላቸው የወጡ ሲሆን ለተለያየ ተግባር የሚዉሉ እና በጥንት አባቶች አጠራር ሽክሽክ አንዳንዴም ኬሻ እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው፡፡

መ.  ሰ.   ረ.  ሸ

ምስል 21፡- ስራው ተጠናቆ ከባና መስሪያው የወጡት ሽክሽክ ልብሶች

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ልብሶች የስራ ሂደታቸው ያላለቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ጥቅጥቅ እንዲሉና እንዲለሰልሱ ንጹህ ውሃ በተጠራቀመበት ቦታ ወይም እቃ ውስጥ መልሶ መላልሶ በመርገጥ ዘርዛራነታቸውን የማጥፋት ተግባር ይከናወናል፡፡ ሽክሽኩ እንዲጠብቅ እና ልስላሴውም እንዲጨምር በአካባቢው በሚገኙት ሬት እና ግሸልጥ (ከመሬት ውስጥ ማስ ማስ ተደርጎ በቀላሉ የሚወጣ ተክል ነው) በተባሉ ተክሎች በደንብ ይታሻል፡፡ ሬት እና ግሸልጥ ሲገባም፣ ሲረገጥም፣ ሰው ሲተካም ወዘተ. የራሱ የተለያዩ ስርአቶች እንዳሉት አባቶች ያስረዳሉ፡፡ ለብርድልብስ፣ ለፎጣ፣ ለመጋረጃ ወዘተ. የሚውሉ አፍሪካ፣ ዳልቻ እና ነጭ የባና ምርቶች የሚረገጡበት ቦታ ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን ለበርኖስ የሚሰራው ጥቁሩ ጨርቅ ከዚህ በፊት

[9] ወንዲፍራው ዘር.ጋባቸው (በርኖስ እና ባና ሰሪ)

ያልተረገጠበት አዲስ ቦታ ተመርጦ እና ሌሎች ቆሻሻዎች ቀለሙን እንዳይረብሹት ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረግለታል። ከዚህ በታች በፎቶዎች ላይ እንደተመለከተው በሁሉም ቦታ ላይ ባግባቡ ተረግጦ ሲያልቅ ስድስት ወይም ሰባት ክንድ ባለው ዱላ ወይም ለስላሳ እንጨት ላይ ተደርጎ ውሃው ይንጠፈጠፋል። ከደረቀ በኋላም እንደሚፈለገው አገልግሎት ስፋት እና ጥበት እየታጠፈ ይሰፋል።



ሀ. ለ. ሐ. መ.

ምስል 22፡- በዕሬት እና በግሽልጥ እየታሸ የተረገጠው ሽክሽክ እንዲደርቅ በባላ ላይ ተሰቅሎ



ሀ. ለ.

ምስል 23፡- ያለቀላቸው የበርኖስ ልብሶች (ጉሬዝማ እና ዳልቻ)

ከዚያም የባና ልብሱ ከእንጨቱ ላይ ይወርድና ንጹህ መስክ ወይም የተስተካከለ ጭንጫ መሬት ላይ ካራቱም ማዕዘን ላይ ተስቦ ወይም ተወጥሮ አራት ትላልቅ ድንጋዮች ይደረጉበታል፤ በተወሰነ ሰዓትም እንዳይጨማደድ እንደገና ይወጠራል። በመጨረሻም የተለያየ ቀለም ያላቸው ጠጠሮች (በአካባቢው አጠራር ግብጣ ይባላሉ) ይጎኑና በርኖሱ ጨርቅ ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል (ፎቶ ግራፍ `ለ`ን ይመልከቱ)። ጠጠር ቆጣሪው ወደ ላይ ጠጠሮችን ሲያጎን ``አዳል ሞቴ፣ ወሰን ጋላ፣ ሽህ አንበሳ፣

ጠቋር፣ እውነቱን አውጣ፣ እውነቱን አሳይ ወዘተ.`` በማለት ድምጹን ከፍ አድርጎ ይናገራል፡፡ በርኖሱ ላይ ያረፈው ጠጠር ነጭ ከሆነ የማህበር ልብስ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከዚያም በምስል 23 “ሐ” ላይ እንደሚታየው የበርኖሱን ዲዛይን ይዞ ይቆረጥ ዘንድ በባለሙያው ይታጠፋል፡፡

ሀ.  ለ. 

ምስል 24[10] ፡- ያለቀላቸው የበርኖስ ልብሶች ከ12 ጠጠሮች ጋር

ከዚህ በታች በፎቶ `መ` ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በዲዛይኑ መሰረት በመቀስ ይቆራረጣል፣ በመጨረሻም `ሰ` ላይ የተመለከተውን ቅርጽ ይይዛል፡፡


ሐ  መ.  ሰ. 

ምስል 25[11] ፡- ተረግጦ ያለቀለት የበርኖስ ልብስ በዲዛይኑ መሰረት ሲቀደድ

በመጨረሻም በበርኖስ ስፌት የተካነ ባለሙያ (ሁሉም ልብስ ሰፊ መስፋት አይችልም) ከዚህ በታች በፎቶዎች ላይ እንደተመለከተው የወንዱን በርኖስ እና የሴቷን መላወሻ (አንዳንዴም ሽርጥ ትባላለች) ይሰራቸዋል፡፡ ሰፊውም ዲዛይኑን ጠብቆ ይሰራል፡፡ ከላይ በ`ሰ` ፎቶ ላይ የበርኖሱ ጨርቅ ሲቆረጥ እንደተመለከተው በግራ በኩል ለብቻዋ ጉብ ብላ ረዘም ያለች ነገር ትወጣለች፡፡ ቁልቁልም ወጥ በሆነ መንገድ ትወርዳለች፣ ካንገቱ ተጠርጎ በግራ በኩል ክፍተት እንዲኖረው ተደርጎ

10 EBS TV, 2019.
11 EBS TV, 2019.

ከትከሻው አጋማሽ አካባቢ ጀምሮ ወደ አንገቱ እስከሚጠጋ ድረስ ለብቻዋ የምትሰራ ዲዛይን አለች፡፡ ይህቺ ዲዛይን ቀድማ ትሰራለች፤ እሷም ከነበረችበት ተቆርጣ ባናው ላይ ባግባቡ ተስተካክላ ትሰፋለች፡፡ በሌላም በኩል ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ነጭ፣ ወደ ቢጫ እና ወደ ጥቁር የወሰደው ቡናማ ወዘተ. ቀለም ባላቸው ማህራረቦች የተለያዩ ጌጦች ይሰራሉ፡፡ እነሱም በርኖሱን ካንገቱ ጀምሮ ወደ ታች እስከሚወርድ ድረስ በበርኖሱ ከውስጥ እና ከውጭ ይዘልቁና መጨረሻ ላይ የተለያዩ ዲዛይኖች እና ጌጦች ተደርጎባቸው ውበትን እንዲላበሱ ይደረጋል (ከዚህ በታች በምስል 24 በ`ሀ` እና በ `ለ` ፎቶ ላይ ይመልከቱ)፡፡ በ`ለ` ፎቶ ላይ እንደሚታየው ሶስት ቁልፍ መሰል ነገር (በአብዛኛው በአረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለሞች ይሰራሉ) ጌጦች ይሰራሉ፡፡ በርኖሱ ዳር ዳሩን በራሱ ድር በስውር ስፌት ዙሪያ ቅምቅሞች ይሰሩለታል፡፡

ሀ.  ለ.  ሐ. 

ምስል 26[12]፡- የተለያየ ዲዛይን ወጥቶለት እና ተሰፍቶ ያለቀለት የበርኖስ ልብስ

በርኖሱ ተሰፍቶ ካለቀ በኋላ ወዲያውኑ አይለበስም፡፡ ጸጉሩ እንዳይረግፍ እና የመኮስኮስ ባህሪውን ለማጥፋት በራሱ አስተጣጠፍ በንጹህ ጨርቅ ይጠቀለልና ትራስ ውስጥ ተቀምጦ ለሁለት ሶስት ወራት ይቆያል፡፡ በዚህ ሂደትም ጸጉሩ ይለሰልሳል፤ ይደመደማል፤ ከመርገፍም ይድናል፡፡ ከዚህ በኋላ እናቶች ለክብረ በዓላት ለብሰው በማሽብሸብ ይዘምራሉ፤ ይጨዋወታሉ፡፡ ይህንን የክብር ልብስ "በላ ልበልሃ" በጥንታዊው ከዚያም በዘመናዊው የፍርድ ቤት ውሎ፣ ለገና፣ ለጥምቀት እና አንዳንዴም ለፋሲካ አባቶች ይለብሱት እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ነገር ግን ባሁኑ ጊዜ ይህ ልብስ በፍርድ ቤትም ሆነ በክብረ በዓላት ጊዜ የመለበሱ ሁኔታ እየቀረ መምጣቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ቀልብ ወይም ዛር ያለባቸው ሰዎች በጥምቀት እና በግንቦት አካባቢ ሲያማቸው በርኖሱን እና መላወሻውን በመያዝ ቀዮ፣ ነጮ፣ ዳልቾ ወዘተ. እያሉ በጭንቅላታቸው ዙሪያ በማዞር "እንትፍትፍ… እንትፍትፍ…" የሚለውን ቃል እየደጋገሙ ሲጨርሱ ያስቀምጡታል፡፡ ከዚህም ሌላ በሀምሌ አካባቢ ላይ ከአቴቴ ጋር የሚያገናኙትም እንዳሉ ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

[12] EBS TV, 2019.

መ.  ሰ  ረ. 

ምስል 27[13]፡- ተዘጋጅቶ ያለቀለት የወንድና የሴት ልብስ

**የእደጥበብ ሙያው በፊት እና አሁን ያለበት ሁኔታ**

የባና እና የበርኖስ ምርት በዚህ ጊዜ ተጀመረ ብሎ ለመናገር ባያስደፍርም ሙያው ረዘም ያሉ አመታትን እንዳስቆጠረ ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሚሰሩት ልብሶች የአካባቢውን ቀዝቃዛ የአየር ንብረት ያማከሉ በመሆናቸው ማንኛውም ፈቃደኛ የሆነ[14] በግብርና የተሰማራ ሰው ሙያውን በአቅራቢያው ካለ ባለሙያ ተምሮ መስራት እንደሚችል የጥናቱ ተተኳሪዎች ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ከብርድልብስ ጀምሮ ፎጣዎችን እና ያልጋ ልብሶችን በባህላዊ መንገድ እየሰሩ ፍላጎታቸውን ያሟሉ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ መሰረታዊ ፍላጎት ከማሟላት አልፎ በአራቱም መንዞች በተለያዩ ባለሙያዎች ይሰሩ የነበሩ የባና እና የበርኖስ ምርቶች ወደ መሀል ሜዳ እና ሞላሌ ከተማ በሚገኙ ገበያዎች እየመጡ የንግድ ልውውጡ ይከናወን እንደነበር አባቶች ይገልጻሉ፡፡ ይህ የንግድ ሂደትም ወደ አዲስ አበባ ብሎም ወደ ኤርትራ ይጓዝ እንደ ነበር በጊዜው የተሳተፉ ሰዎች ይናገራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ሙያ የተሰማሩ እና በኋላም ወደ ንግድ ልውውጡ የሄዱ ሰዎች ሲናገሩ፡-

> በፊት በፊት ከበጎች አጠባ ጀምሬ ባናውን እየሰራሁ ስሸጥ ቆየሁ። በ1968 ዓ.ም ደግሞ ባናውንም እየሰራሁና እየረገጥኩ ለአካባቢው ነጋዴዎች አስረክብ ነበር፤ ቀስ በቀስም ወረቴ እየሰፋ ሲሄድ እኔ መስራቴን ትቼ ከሌሎች ባለሙያዎች እየገዛሁና እየተረከብኩ ወደ አዲስ አበባ መጫን ጀመርኩ፤ ቀጥሎም የንግድ ልውውጡን በማስፋት ከአስመራ ሰዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በመፍጠር ምርቱ ወደ ኤርትራ እንዲገባ አደርግ ነበር። በዚያም በርካታ ደንበኞች አፍርቸ እኔው ራሴ እስከ ከረን ድረስ በመሄድ የባና ምርቱን በመሸጥ ከፍተኛ ልምድ እና ገቢ አካብቻለሁ። በዚያን ጊዜ የኤርትራ ነጋዴዎች የባና ምርቱን በተሽከርካሪ መኪናዎችም ሆነ ባውሮፕላን

[13] EBS TV, 2019.

[14] እንደ ሸማ፣ ቆዳ እና ሸክላ የዕደጥበብ ስራ በተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ማንኛውም ሰው በቀላሉ ስራውን ለምዶ ሊሰራው እንደሚችል ከመስክ የተሰበሰበው መረጃ ያመለክታል፡፡

በወኪሎቻቸው አማካኝነት ተጭኖ ይሄድ እንደነበረም አስታውሳለሁ ብለዋል፡፡[15]

ከኤርትራ ጋር በነበረው የንግድ ልውውጥ የተሳተፉት ሌላው የጥናቱ ተተኳሪ እንደገለጹት ደግሞ፡-

> ምርቱን ከመሃል ሜዳ ከሰበሰብን በኃላ ከአስመራ ሰዎች እና ከሌሎች ነጋዴዎች ጋር እንገናኝ የነበረው አዲስ አበባ በሚገኘው አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ነበር፡፡ ግብይቱ የሚከናወነው መኮንን ነጋሽ የተባሉ ባለሀብት በሰጡን ቦታ ላይ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የነበሩ ነጋዴዎች የሚገዙን ለተለያየ አገልግሎት የሚውለውን የባና ምርት ነው፤ የበርኖስ ልብሱ ግን ባካባቢው ገበያ ተወስኖ ይሸጥ ነበር በማለት አስረድተዋል፡፡[16]

በተጨማሪም እንደ ብርድልብስ እና እንደ ፎጣ የተሰራውን የባና ምርት የኤርትራ ሴቶች ሰውነታቸው ይጠራ ዘንድ የተለያዩ ጭሳጭሶችን በውስጡ ሆነው እንደሚታጠኑበት እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ደግሞ እንደ ያልጋ ልብስ፣ ብርድልብስ፣ ፎጣ፣ ሹራብ፣ የጣውላ መወልወያ ወዘተ. ይጠቀሙበት እንደነበር የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የነበረውን የንግድ ሂደት አንድ ተጠኚ[17] ሲናገሩ፡- ``የዚያን ጊዜ የነበረው የስራ እና የገቢ ሁኔታ ጥሩ ነበር፤ ቀስ በቀስ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ስትገነጠል ሁሉም ነገር ቀረ`` ብለዋል፡፡ እኒህ አባት የስራው ክንዋኔ ትዝታ ይሆናቸው ዘንድ የንግድ ልውውጡን ከመሀል ሜዳ ተነስቶ አዲስ አበባ ብሎም ወደ አስመራ በተሽከርካሪዎች ሲጓዝ የሚያሳይ ስዕል ከቤታቸው ግድግዳ ላይ ተቀምጦ ይታያል (ምስል 26ን ይመልከቱ)፡፡



ምስል 28፡- የባናው ምርት የጉዞ ሁኔታን የቃኘ ስዕል[18]

---

[15] አቶ በላይ አብቹ (ባና ሰሪ እና ነጋዴ)
[16] አቶ ጸጋው ሲገኝ (ባና ሰሪ እና ነጋዴ)
[17] አቶ በላይ አብቹ (ባና ሰሪ እና ነጋዴ)
[18] ከአቶ በላይ አብቹ ቤት ግድግዳ ላይ የተገኘ

ምርቱ በደርግ ዘመነ መንግስት የአካባቢው ሰዎች በአግባቡ እንዲጠቀሙበት በዩኒሴፍ እና በወርልድ ቪዥን እርዳታ ማህበር ተቋቁሞ ስራው ይከናወን እንደነበር የአካባቢው አባቶች ይናገራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ለሰራተኞች ደሞዝ እና የእርዳታ ስንዴ በመስጠት ስራው ከተሰራ በኋላ በተለያየ ቦታ ምርቱን ለማህበረሰቡ ለማቅረብ ተሞክሮ ነበር፡፡ ነገር ግን በነበረው የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት እንደተቋረጠ ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

በመቀጠልም በኢህአዴግ ዘመነ መንግስት የደሃ ደሃ የሆኑ የማህበረሰቡ ክፍሎች ተለይተው እና ተሰባስበው ስራው ለተወሰነ ጊዜ እንዲቀጥል ከተደረገ በኋላ አዋጪ አይደለም ተብሎ እንደገና እንደተዘጋ በሂደቱ ያለፉ ሰዎች ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በኋላም በ1992 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሴቶች እደጥበባት ማዕከል እንደገና ሴቶችን በማሰባሰብ የበጎች ጸጉር እየቀረበላቸው፣ ፈትለው ሲጨርሱም በኪሎ 15 ብር እየተከፈላቸው የተለያዩ ዲዛይን ያላቸው ምንጣፎች፣ ያልጋ ልብሶች፣ የእግር መረገጫዎች ወዘተ. ይሰሩ እንደነበር በዚያን ጊዜ የማዕከሉ ተቆጣጣሪ የነበሩ አንድ አባት ይገልጻሉ፡፡ ይህም ሂደት ለተከታታይ አምስት አመታት ሲሰራ ቆይቶ እንደገና አዋጪ አይደለም ተብሎ ተዘግቷል፡፡

ከዚህ በኋላም ወርልድ ቪዥን የባና እና የበርኖስ የማምረቻ ቦታ እንዲሁም የስጋጫ ወይም የእግር ምንጣፎች መስሪያ ጣውላዎችን በማዘጋጀት የተለያዩ የውጭ ዜጋዎችን በማምጣት ባለሙያዎችን ያሰለጥን እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የሰለጠኑ ሰዎችም በጎልማሶች ማሰልጠኛ ጣቢያ (ጎማጣ) በኩል ለሌሎች ሰዎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ምቹ ሁኔታዎች ቢፈጠሩም ስራው አዋጪነት የለውም በሚል በርካታ ባለሙያዎች ወደ ግብርናቸው ተመልሰው ገብተዋል፡፡ ለዚህ ተብሎ የተሰራው የእደጥበብ ማዕከልም በፎቶው ላይ እንደተመለከተው አስታዋሽ አጥቶ ይገኛል፡፡





ምስል 29፡- ወርልድ ቪዥን ያሰራው የባና እና የበርኖስ የማምረቻ ቦታ

ከዚህም በተጨማሪ ልማዳዊ ምርቱ በዘመናዊ አልባሳት በመቀየሩ፣ ድካሙ እና ገቢው ባለመጣጣሙ ምክንያት አብዛኛው ባለሙያ የሚሰራበትን እቃ ሰቅሎ የግብርናውን ስራ እያከናወነ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ ወደ ሌሎች ስራዎች እንደተሰማሩ ከዚህ በታች ያሉት ምስሎች ያመለክታሉ፡፡



ምስል 30፡- የባና እና የበርኖስ ባለሙያዎች ስራውን ማቋረጣቸውን የሚያሳዩ ፎቶዎች

በሌላም በኩል በዚህ ሙያ ላይ የተሰማሩ የተወሰኑ ሰዎች ነባሩን የመስሪያ እቃ በተወሰነ መልኩ በማስተካከል የሽመናውን ስራ በቀላሉ ለምደው እንደሚሰሩት፣ ከበፊቱ የበለጠ እንደሚያፈጥናቸው እና ከፍተኛ የገቢ ምንጭ እንደሚያገኙበት ይናገራሉ፡፡

> ``ዝተት መስራቱን ያቆምኩት ሶስት አመት አልፎኛል፤ አሁን የምሰራው ሸማ ነው፤ የባና ስራውን ያቆምኩት ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ነው፡፡ ዝተቱ እንደሸማው አይከፍትም፤ ስትሰራው እና ስትወረውረው እንደ ሸማው በቀላሉ አይሽከረከርም፤ ምክንያቱም ክሮቹ የመያያዝ ባህሪ ስላላቸው ቶሎ ቶሎ አያፈጥንም፡፡ እኔ አንድ ኩታ በአንድ ቀን ቆርጨ ማውጣት ስችል በዚሁ ልክ የሆነውን በርኖስ ለመጨረስ ግን ሁለት ቀን ይፈጅብኛል፡፡ በዚህም ምክንያት በርካታ የማውቃቸው ወዳጆቾ የባና እና የበርኖስ መስሪያ እቃቸውን ወደ ሸማው ቀይረዋል፡፡[19]

## በባና እና በበርኖስ የስራ ሂደት ላይ የሴቶች እና የወንዶች ሚና

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለመጥቀስ እንደተሞከረው በስራው ሂደት ውስጥ የሴቶች እና የወንዶች ድርሻ የተለያየ ነው፡፡ ሴቶች የተሸለተውን የበጎች ጸጉር በእጅ ያፍታታሉ፤ ጸጉሩ የበለጠ እንዲለሰልስ ደጋን በሚባለው መሳሪያ ይነድፋሉ፤ ጸጉሩን በመዳመጥ ያባዝታሉ፤ ይፈትላሉ፤ ከግራ ወደ ቀኝ እና ከቀኝ ወደግራ ያከራሉ፤ ክሩን በልቃቂት መልክ ያዘጋጃሉ፤ የሁለቱን ልቃቂት ጫፍ በመያዝ እና በማጠንጠን ይኮባሉ፤ የኮቡትንም ኩብ ወደኃላ በማክረር እንዝርት በተባለችዋ መሳሪያ ያጠነጥናሉ፡፡ ወንዶች ደግሞ ከበጎች መረጣ ጀምሮ በንጹህ የወንዝ ውሃ ጸጉራቸውን ያጥባሉ፤ ጸጉሩ በሚደርቅበት ጊዜ ይሸልታሉ ወይም ይቆርጣሉ፤ድሩን በመድራት በትናንሽ ቀሰሞች ያጠነጥናሉ፤ መኑን አዘጋጅተው በመቋጠር ይቆጥራሉ፤ የባና እና የበርኖስ ልብሱን ሰርተው በማጠናቀቅ ሸክሸኩን በንጹህ ውሃ፣ በሬት እና በግሽልጥ በተዘጋጀለት ቦታ መልሶ መላልሶ በመርገጥ ክፍተቱ እንዲጠቀጠቅና እንዲለሰልስ

---

[19] ወንዲፍራው ዘርጋባቸው (ባና ሰሪ)

ያደርጋሉ፤ በመጨረሻም ልብሱን በባላ ላይ በማንጠፍጠፍ እንዲደርቅና ለመልበስ ዝግጁ እንዲሆን ለልብስ ሰፊ ባለሙያ ይሰጣሉ።

በሌላም በኩል ደግሞ በባና እና በበርኖስ ስራ የተሰማሩት አብዛኛው ባለሙያዎች እንደ ሸማ፣ ቆዳ እና ሸክላ ሙያ የእደ-ጥበብ ስራውን የለመዱት ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ሳይሆን ከጓደኞቻቸው፣ ከአማቾቻቸው፣ ከጎረቤት እና ከወዳጅ ዘመዶቻቸው እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። በመሆኑም በርካታ ሰዎች ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ሲሉ ከግብርና ስራቸው ጎን ለጎን በስራው ላይ የተሰማሩ ሰዎችን በማገዝ ሂደት እንደጀመሩት ይገልጻሉ።[20] ስራው በተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የተገደበ ባለመሆኑ በዚህ ሙያ የሚሰማሩ ሰዎች በሌሎች ነዋሪዎች ዘንድ የመገለል እድላቸው አነስተኛ መሆኑን ከጥናቱ ውጤት መረዳት ይቻላል።[21]

## 5. ማጠቃለያ እና ይሁንታ

በመንዝ አካባቢ የሚሰራው የባና እና የበርኖስ ምርት የአካባቢው ማህበረሰብ የጥበብ፣ የማንነት፣ የእምነት፣ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች መገለጫ ቢሆንም የመጥፋት አደጋ እንደተጋረጠበት የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ከዚህም ሌላ በሙያው አንቱ የተባሉ ሰዎች የእድሜያቸው መግፋት እና ወደ ሞት መቃረብ፣ ከአብራካቸው የወጡ ልጆችም ለሙያው የሚሰጡት ክብር እና ትኩረት አናሳ መሆን ስራውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር፣ ጠብቆ ለማቆየት እና ወደፊትም ለማስቀጠል አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ልማዳዊ የባና እና የበርኖስ ምርቶች የተለየ የቁሳቁስ ግብዓት፣ መገልገያ መሳሪያዎች፣ የአሰራር ሂደቶች፣ የአከዋወን ስርአቶች፣ ለተግባሩ መፈጸሚያነት የሚውሉ ስነቃላዊ ግጥሞች፣ የተለያዩ ብልሃቶች እና ክሂሎች ያሏቸው አገር በቀል የእደ-ጥበብ ሙያዎች ቢሆኑም ለበርካታ ዘመናት ምንም አይነት የቴክኖሎጂ መሻሻል ሳይደረግባቸው እየተከናወኑ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። የስራው ሂደትም ጥንታዊ፣ አድካሚ፣ አሰልቺ እና በቂ ገቢ የማያስገኝ በመሆኑ የምርት ሂደቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ ከመምጣቱም ባሻገር ነባር ባለሙያዎችም ወደ ሌላ ሙያ በመሰማራት ላይ ይገኛሉ። ነገር ግን ባደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ያሉ በርካታ ጥቃቅን፣ መሀከለኛ እና ትላልቅ የንግድ ተቋማት የልማዳዊ አገር በቀል እውቀት ቅርሶችንም ሆነ ቁሶችን በመጠቀም እና በማዘመን ከፍተኛ ገቢ በመሰብሰብ ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ ፤ ነገር ግን ፈጠራው እና የአዘማመን ሁኔታው ከሚገባው በላይ ተጋኖ ባህላዊ ገፅታውን እንደይሸረሽረው ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል (WIPO Publication No. 913, p. 6)። በተጨማሪም ድህነት፣ ስራ አጥነት እና ተመጣጣኝ የገቢ አሰረጫጨት ችግር ባለባቸው ታዳጊ አገራት ውስጥ ልማዳዊ የእደ-ጥበብ ስራዎችን ወደ አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች ከፍ የማድረግ ብልሃትን መጠቀም አይተኬ ሚና እንዳለው M. Terry (2017) ያስረዳሉ።

[20] አባ ገብረህይዎት ባዬ፣ አረጋ በጋሻው፣ ወንዲፍራው ዘርጋባቸው እና በላይ አብቹ (ባና ሰሪዎች)

[21] አቶ አድማሴ በነበሩ እና አቶ ጸጋው ሲገኝ (ባና ሰሪ እና ነጋዴ)

በመሆኑም እንዲህ አይነት ጥበባዊ እና ልማዳዊ የእውቀት መገለጫዎች ለማህበረሰቡ ካላቸው ማህበራዊ፣ መንፈሳዊና ባህላዊ ፋይዳ በተጨማሪ የፈጠራ ኪን ምንጭ በመሆን ለኢኮኖሚያዊ እድገት እና ለኢንዱስትሪዎች መነሳሳት እንደሚያገለግሉ ተገንዝቦ ሰፊ ስራ መስራት አለበት (World vision, 2000)፡፡ ከዚህም ሌላ ባህላዊ ቁሶችን ለዘመኑ ፈጠራ መነሻ በማድረግ የማህበረሰብ አቀፍ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም፣ አካባቢያዊ ስራ በመፍጠር፣ የባለሙያዎችን ክሂሎት በማሳደግ፣ ተገቢ የቱሪዝም እድል በመፍጠርና ማህበረሰቡ ከሚያመርተው ምርት የውጪ ገቢ በማስገኘት ለኢኮኖሚያዊ እድገቱ አስተዋፅዖ እንዲያበረክት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ስለዚህ ይህንን አገር በቀል እውቀት ጠብቆ ለማቆየት፣ ለማስቀጠል፣ ዘመናዊ አሰራርን እንዲከተል እና ማህበረሰቡም በዚህ ሙያ ገቢውን ያሳድግ ዘንድ በርካታ የባለድርሻ አካላት የነቃ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከእነዚህም መካከል ግንባር ቀደሞች በአካባቢው ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው፡፡ በስራው ከፍተኛ ልምድ ካካበቱ አቻ ዩኒቨርሲቲዎች እና አገሮች ጋር የልምድ ልውውጥ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ የመሸተት እና የመኮስኮስ ባህሪውን ለማስቀረት ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የባህል እና ስፖርት እንዲሁም የቱሪዝም ሚኒስትር መስሪያ ቤቶች በእደጥበብ ላይ ከሚሰሩ መንግስታዊ የሆኑ እና ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር እንዲሁም ከተለያዩ ያገር ውስጥም ሆነ አለም አቀፍ ዲዛይነሮች ጋር በመተሳሰር ህልውናውን አጠናክሮ የማስቀጠል እና ምርቱንም የማስተዋወቅ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ የክልል፣ የዞን፣ እና የወረዳ ግብርና ቢሮዎች ደግሞ ጸጉር ያላቸው የበጎች ምርጫ ከፍ እንዲል የማዳቀል ስራ በሰፊው እንዲሰራ ጥረት ቢያደርጉ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በተለይም ለበርኖስ ስራ የሚሆኑ ጥቁር በጎች በአካባቢው እየጠፉ በመሆኑ እነሱን በብዛት የማርባት እና ጥራታቸውም የተጠበቀ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

ባጠቃላይ በዚህ ልማዳዊ የእደ-ጥበብ አሰራር ሂደት ላይ የተገኘውን የምርምር ውጤት መሰረት በማድረግ፣ ሙያውን ዘመኑ ባፈራቸው ቴክኖሎጅዎች ለማሳደግ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ሙያው ለማህበረሰቡ የበለጠ ጥቅም እንዲሰጥ ሰፋ ያለ ፕሮጀክት በመቅረጽ፣ የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸውን ልማዳዊ የባና እና የበርኖስ ምርቶች ጨርሶ እንዳይጠፉ የመታደግ፣ የማህበረሰቡን ጥበብ እና ማንነት ጠብቆ የገቢ ምንጫቸውም ጎን ለጎን የማሳደግ፣ ከኤርትራ ጋር የነበረውን የንግድ ልውውጥም እንደገና የማስቀጠል፣ የምርት ጥራቱን የመጠበቅ እና በሌሎች አገሮች የሚኖረውንም ገበያ የመፈተሽ ስራ መስራት እንዳለበት ጥናቱ ያመላክታል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

**ፈቃደአዘዘ፣ 1991። የስነ-ቃል መምሪያ። አዲስአበባ። ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረጃ ተቋም።**

Adedamola, Adetiba, 2017. Endangered Culture and Identity in the 21st Century: The Esan and other Nationalities in Nigeria. H-Net: Humanities and social sciences Online- H-Africa.Available at http://networks.h-net.org/node/491027/pdf

EBS TV, 2019. Semonun Addis Ethiopian Bernos Worn By Fathers. **ሰሞኑን አዲስ የበርኖስ ልብስ አዘገጃጀት በደብረብርሐን ልዩ ፕሮግራም** https://www.youtube.com/watch?v=5wvdKmPBOKA&t=1105s

Goldstein, Kenneth. 1964. A Guide for Field Workers in Folklore.American Folklore Society by Folklore Associates, INC.

Hale, K. (1998). On endangered languages and the importance of linguistic diversity. In *Endangered Languages;Language Loss and Community Response,* 192-216, ed. by Lenore A, Grenoble and Lindsay J. Whaley. Pp.. Cambridge: Cambridge University Press.

Ihatsu, A. M. (2002). Making sense of contemporary American craft. Academic dissertation. University of Joensuu, Publications in Education. 73.

Krueger RA, 1994. Focus Groups: A Practical Guide for Applied Research. Thousand Oaks, CA: Sage Publications.

M. Terry, Elizabeth, 2017.  The Economic and Social Significance of the Handicraft industry of Botswana, PhD Thesis, The school of Oriental and African Studies. University of London, London. Stable URL: https://eprints.soas.ac.uk/28824/1/10672993.pdf

Prown, J. David, 1982. Mind in Matter: an Introduction to Material Culture Theory and Method. Winterthur Portfolio, Vol. 17, No. pp. 1-19: The University of Chicago Press. Stable URL: http://www.jstor.org/stable/1180761

Sims, Martha C. and Martine Stephens, 2005. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions, Utah: Utah State University Press.

UNESCO Ad Hoc Expert Group on Endangered Languages (2003). "Language Vitality and Endangerment http://www.unesco.org/culture/ich/doc/src/00120-EN.pdf .

World Intellectual Property Organization (WIPO). Intellectual Property Traditional Cultural Expressions /Folklore. WIPO Publication https://www.wipo.int/edocs/pubdocs/en/tk/913/wipo_pub_913.pdf.

World Vision Ethiopia. 2000. Food Security Monitoring Report of November 1999. Grants division Addis Ababa.

## አባሪ

## የጥናቱ ተሳታፊዎች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | የመኖሪያ አድራሻ | | የስራ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወረዳ | ቀበሌ | |
| 1 | አባ ገብረህይዎት ባዬ | ወ | 67 | መንዝ ጌራ ፣ መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ |
| 2 | አቶ አረጋ በጋሻው | ወ | 72 | መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ |
| 3 | አቶ በላይይሁን ዘአማኑኤል | ወ | 70 | መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ |
| 4 | አቶ በላይ አብቹ | ወ | 78 | መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ እና ነጋዴ |
| 5 | አቶ ጸጋው ሲገኝ | ወ | 68 | መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ እና ነጋዴ |
| 6 | አቶ ይታገሱ ላቀው | ወ | 52 | መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ |
| 7 | አቶ ማሞ ለጋው | ወ | 72 | መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ |
| 8 | ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ገስጤ | ሴ | 70 | መሃልሜዳ | 020 | ፈታይ |
| 9 | ወ/ሮ አስማረች መንገሻ | ሴ | 55 | መሃልሜዳ | 020 | ፈታይ |
| 10 | አቶ ወንዲፍራው ዘርጋባቸው | ወ | 69 | መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ |
| 11 | ጌታነህ ገብረየስ | ወ | 74 | መሃልሜዳ | 020 | ባና ሰሪ |
| 12 | አቶ አስቻለው ተፈረደኝ | ወ | 65 | መሃልሜዳ | 02 | ባና ሰሪ |
| 13 | አቶ ታደለ በላይይሁን | ወ | 79 | መሃልሜዳ | 02 | ባና ሰሪ |
| 14 | አቶ ሃብት ይመር ዳምጠው | ወ | 67 | መሃል ሜዳ | 02 | ባና ሰሪ |
| 15 | አቶ ዳምጠው ጌታሁን | ወ | 70 | መሃል ሜዳ | 02 | ባና ሰሪ |
| 16 | አቶ ወልደ ሃና አጎናፍር | ወ | 55 | መሃል ሜዳ | 02 | ባና ሰሪ |
| 17 | አቶ አድማሴ በነበሩ | ወ | 35 | መንዝ ማማ፣ ሞላሌ | 06 | የባህል/ቱ ባለሙያ |
| 18 | አቶ አማረ ሃይሌ | ወ | 73 | ሞላሌ | 06 | ባና ሰሪ |
| 19 | አቶ ግርማ ማሞ | ወ | 68 | ሞላሌ | 06 | ባና ሰሪ |
| 20 | አቶ ሸዋንእዘዝ ተፈራ | ወ | 71 | ሞላሌ | 06 | ባና ሰሪ |
| 21 | ቄስ ተመሰለው ጥላዬ | ወ | 76 | ሞላሌ | 06 | ባና ሰሪ |
| 22 | ወ/ሮ ወርቅነሽ ከሳቴ | ሴ | 65 | ሞላሌ | 06 | ፈታይ |
| 23 | ወ/ሮ ሙሉነሽ ገ/ዮሃንስ | ሴ | 60 | ሞላሌ | 06 | ፈታይ |
| 24 | ወ/ሮ አሰለፈች ኃ/ማርያም | ሴ | 57 | ሞላሌ | 06 | ፈታይ |
| 25 | አቶ አየናቸው አደናግር | ወ | 68 | ሞላሌ | 02 | ባና ሰሪ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 26 | አቶ ወንዲፍራው ዘርጋባቸው | ወ | 63 | ሞላሌ | 02 | ባና ሰሪ |
| 27 | አቶ ደመላሽ ተፈራ | ወ | 66 | ሞላሌ | 02 | ባና ሰሪ |
| 28 | ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ገስጤ | ሴ | 55 | ሞላሌ | 02 | ፈታይ |
| 29 | አቶ ማሞ አርጋው | ወ | 71 | ሞላሌ | 02 | ባና ሰሪ |
| 30 | አቶ አንዳርጋቸው ገ/ማርያም | ወ | 59 | ሞላሌ | 02 | ባና ሰሪ |
| 31 | አቶ ዳኜ ነቄ | ወ | 53 | ሞላሌ | 02 | ባና ሰሪ |
| 32 | አቶ ግዛው ማሞ | ወ | 62 | ሞላሌ | 02 | ባና ሰሪ |
| 33 | አቶ ጌታነህ ገብሬ | ወ | 78 | ሞላሌ | 02 | ባና ሰሪ |